# የግብፅ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ፣ የወደፊት አቅጣጫ እና ጂኦ-ፖለቲካዊ እንደምታ

( ብሩክ መኮንን)

ግንቦት 2004 ዓ.ም

## መግቢያ

እ.ኤ.አ በጥር ወር 2011 የተጀመረው የግብፅ አብዮት ሶስተኛና ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡ የአብዮቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ህዝባዊው አመፅ ከተቀሰቀሰበት እ.ኤ.አ ጥር ወር 2011 ጀምሮ ፕሬዚዳንት ሙባረክ ከስልጣን እስከተወገዱበት ወቅት ድረስ የተፈጠሩትን ፖለቲካዊ ክስተቶች ሲያካትት ሁለተኛው ምዕራፍ በግብፅ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው ዴሞክራሲያዊ የፓርላማ ምርጫ የተካሄደበት፣ የእስልምና እምነት አራማጅ ፓርቲዎች አብላጫ የፓርላማ መቀመጫዎችን ያገኙበት እንዲሁም የሀገሪቱን ህገ መንግስት ለማርቀቅ በተቋቋመው የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤት ዙሪያ የተነሱ እሰጥ አገባዎችን የሚመለከት ነው፡፡

ሶስተኛውና በብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ወሳኝና የግብፅን የወደፊት አቅጣጫ ይወስናል ተብሎ እየተገለፀ የሚገኘው ምዕራፍ እ.ኤ.አ ግንቦት 23 እና 24 ቀን 2012 የሚደረገው የመጀመሪያው ዙር እንዲሁም እ.ኤ.አ ሰኔ 16 እና 17 ቀን 2012 የሚደረገው ሁለተኛ ዙር ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ነው፡፡

## የግብፅ የፓርላማ ምርጫ ውጤት

በግብፅ አብዮት ሁለተኛ ምዕራፍ ላይ በዐቢይነት የሚጠቀሱት ሁለት ጉዳዮች የፓርላማ አባላት ምርጫ እና የግብፅን ህገ መንግስት ለማርቀቅ የሚያስችል ምክር ቤት የማቋቋም ተግባራት ናቸው፡፡

የግብፅ የፓርላማ አባላት ምርጫ እ.ኤ.አ ከህዳር 28 ቀን 2011 ጀምሮ እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት ወር 2012 ድረስ በተለያዩ ዙሮች ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በዚህም ለረጅም ጊዜ የነበረውን ልምድ እና ጠንካራ አደረጃጀት በመጠቀም Freedom and Justice Party በሚል አዲስ ስያሜ ወደ ምርጫ ውድድሩ ብቅ ያለው የMuslim Brotherhood 47.2 በመቶ እንዲሁም በSalafist የእስልምና እምነት አራማጆች የሚመራው Al-Nour ፓርቲ 24.3 በመቶ በማምጣት፣ በአጠቃላይ በእስልምና እምነት

የሚመሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ወደ 71 በመቶ የሚደርሰውን የፓርላማ መቀመጫ ለማሸነፍ ችለዋል፡፡

ከፕሬዚዳንት ሙባረክ አገዛዝ ውድቀት ጀምሮ የግብፅን የሥልጣን መንበር የተቆጣጠረው የወታደራዊው ምክር ቤት ስልጣኑን በተረከበበት ወቅት ይፋ ባደረገው ዕቅድ፤ በመጀመሪያ የፓርላማ ምክር ቤቶች ምርጫን፣ በመቀጠል ህገ-መንግስት የማርቀቅና በመጨረሻም ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እንዲደረግ በማድረግ ስልጣኑን በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ለማስረከብ ቃል መግባቱ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ከፓርላማ ምክር ቤቶች ምርጫ ውጤት ማግስት ጀምሮ በፓርላማ ምርጫው ከሚመረጡ የምክር ቤት አባላት መሀከል 100 የሚሆኑትን በመምረጥ ህገ መንግስቱን የማርቀቁን ሂደት ለመጀመር እንቅስቃሴ የተጀመረ ቢሆንም ይህ እንቅስቃሴ ከፍተኛ እንቅፋት አጋጥሞት በታሰበለት ዕቅድ መሠረት ተግባራዊ መሆን አልቻለም፡፡

## ህገ መንግስት በማርቀቅ ሂደት የተፈጠሩ አለመግባባቶች

የወታደራዊው ምክር ቤት እ.ኤ.አ በመጋቢት ወር 2011 ይፋ ባደረገው የህገ መንግስት ድንጋጌ /constitutional declaration/ ሁለቱ የፓርላማ ምክር ቤቶች ቅርንጫፎች በጋራ የሀገሪቱን ህገ መንግስት የሚያረቅና አንድ መቶ አባላት ያሉት የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን እንዲያቋቁሙ ደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከህግ አኳያ የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽኑን አወቃቀር የመወሰን ሥልጣን ለሁለቱ ምክር ቤቶች መሠጠቱን መነሻ በማድረግ የምክር ቤት አባላቱን የመሰየም ተግባር ተከናውኗል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የምክር ቤት አባላት ስያሜ የኃይማኖት መሠረት ከሌላቸው ፓርቲዎች /Secular parties/ እንዲሁም ከግል ተወዳዳሪዎች ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡

እነዚሁ የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽኑን አወቃቀር የሚቃወሙ አካላት በዋናነት የሚያነሱት ስጋት የእስልምና እምነት አራማጅ የሆኑ ፓርቲዎች በፓርላማ

ውስጥ ካገኙት አብላጫ መቀመጫ የተነሳ በኮሚሽኑ ከፍተኛውን ቁጥር በማግኘት በሚረቀቀው ህገ መንግስት ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚለው ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህንኑ ስጋት ለማስወገድም የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ በዋናነት ከፓርላማ ውጪ ከሚገኙ እንደ የኃይማኖት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሙያ ማኅበራት... ወዘተ ከመሳሰሉና የግብፃውያንን ፍላጎት በተሻለ ሊያንፀባርቁ ይችላሉ ከተባሉ ተቋማት እንዲውጣጡ ሲጠይቁ ቆይተዋል፡፡

በአጠቃላይ በግብፅ የፖለቲካ መድረክ ተዋናይ የሆኑ አካላት የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱን በተመለከተ ሶስት አይነት አካሄዶችን ሲያንፀባርቁ መቆየታቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህም፡-

- በMuslim Brotherhood የሚመራው የነፃነትና የፍትህ ፓርቲ /Freedom and Justice Party/ 40 የምክር ቤቱ አባላት የፓርላማ ተመራጮች መሆን አለባቸው፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በም/ቤቱ ባላቸው መቀመጫ መሠረት ይህንኑ ድርሻ ሊከፋፈሉ ይገባል የሚል አቋም ሲያራምድ ቆይቷል፡፡ ፓርቲው በተጨማሪም 30 የምክር ቤቱ አባላት ከፓርላማው ውጪ የሆኑና በቀጥታ በፓርላማው የሚመረጡ መሆን እንዳለባቸው፤ ቀሪዎቹ 30 አባላት ደግሞ በሙያ ማህበራት፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ በፖሊስ፣ በጦር ኃይሉ፣ በግብፃውያን ዲፕሎማቶች፣ በሰራተኛ ማህበራት፣ በዳኞች እና በCoptic ቤተክርስቲያን የሚመረጡ እንዲሆኑ አቋም ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ፓርቲው አብላጫ የፓርላማ ድምጽ ከማግኘቱ አንፃር ይህ አቋም በህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ ውስጥ የተሻለ ተሰሚነት እንዲያገኝ እንዲሁም ህገመንግስት በማርቀቁ ሂደት የራሱን ተፅዕኖ ለማሳረፍ ያስችለዋል የሚሉ ተቃውሞዎች ሲቀርቡበት ቆይተዋል፡፡

- የሳላፊ እምነት አቀንቃኝ የሆነው al-Nour Party በበኩሉ የፓርላማ ተመራጮች በህገ መንግስት የማርቀቅ ሂደት ውስጥ ጠንካራ ሚና መጫወት የሚችሉበት ዕድል ሊኖራቸው እንደሚገባ አቋም ሲያራምድ ቆይቷል፡፡ ፓርቲው በተጨማሪም የሚረቀቀው ህገ መንግስት የግብፅን እስላማዊ መለያ /Islamic Identity/ በግልፅ የሚያስቀምጥና እስላማዊ ህግ የህገ መንግስቱ ማዕከል መሆን ይገባዋል የሚል ጠንካራ አቋም አራምዷል፡፡ የፓርቲ አቋም በሌሎች ኃይማኖታዊ መሠረት በሌላቸው ፓርቲዎች /Secular Parties/፣ በCoptic ቤተክርስቲያን ተከታዮችና በሊበራል አስተሳሰብ አራማጆች ዘንድ ከፍተኛ ስጋትን ሲፈጥር ተስተውሏል፡፡
- ኃይማኖታዊ መሠረት የሌላቸው /Secular/ ፓርቲዎችና ግለሰቦች /personalities/ በፓርላማዎቹ ውስጥ ካላቸው ከሃያ አምስት በመቶ ያልበለጠ ውክልና የተነሳ እስላማዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ፓርቲዎች በህገ መንግስቱ ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉትን ተፅዕኖ ለመገደብ በማሰብ የፓርላማ አባላት በህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ ውስጥ የሚኖራቸው ውክልና የተገደበ እንዲሆን ተንቀሳቅሰዋል፡፡ እነዚህ አካላት በአንፃሩ የሙያ ማህበራት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሠራተኛ ማህበራት፣ የፍትህ አካላት … ወዘተ በምክር ቤቱ ውስጥ የሚኖራቸው ውክልና የሰፋ እንዲሆን አጥብቀው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሶስት ዋና ዋና አቋሞች ሊያስታርቁ ይችላሉ የተባሉ ሀሳቦች በግል ተወዳድረው የፓርላማ መቀመጫ ካገኙ አባላት፣ የወታደራዊውን ምክር ቤት ወክለው የፓርላማ መቀመጫ ካገኙ አባላት እንዲሁም የፓርላማ መቀመጫ ማግኘት ካልቻሉ ፓርቲዎች ዘንድ የቀረቡ ሲሆን በአጠቃላይ እነዚህ መነሻ ሀሳቦች የጋራ ማጠንጠኛ ሀሳብ ፓርላማው የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤት አባላትን በመምረጥና ህገ መንግስት በማርቀቅ ሂደት ውስጥ የሚኖረው ሚና እጅግ የተገደበ መሆን አለበት የሚል መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ በተለያዩ ወገኖች የተንፀባረቁ ተቃውሞዎች በቀጠሉት ሁኔታ እ.ኤ.አ መጋቢት 24 ቀን 2012 ይፋ በተደረገው የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤት

አባላት ምርጫ ሁለቱ ምክር ቤቶች በጋራ 100 አባላትን የሰየሙ ሲሆን፣ 50ዎቹ አባላት ከፓርላማ ምክር ቤቶቹ የተቀሩት 50 አባላት ደግሞ ከፓርላማዎቹ ውጪ እንዲሆኑ መደረጉን ይፋ አድርገዋል፡፡

ከ50ዎቹ ተመራጭ የፓርላማ አባላት መሀከል 36 ያህሉ የFreedom and Justice Party እና የal-Nour ፓርቲ አባላት ሲሆኑ ከፓርላማ ውጪ የተመረጡት 50 አባላት ምንም እንኳን እራሳቸውን የህግ ባለሙያዎች፣ ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው ምሁራን /independent thinkers/ ወዘተ አድርገው ቢያቀርቡም በብዙዎች ዘንድ የእስልምና የፖለቲካ አስተሳሰብ አራማጆች እንደሆኑ ሲገለፅ ቆይቷል፡፡

ይህ ሁኔታ በሌሎች ኃይማኖታዊ መሠረት በሌላቸው ፓርቲዎችና ግለሰቦች እንዲሁም በሊበራል አስተሳሰብ አራማጆች ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ያስከተለ ሲሆን ወደ ሃያ አምስት የሚጠጉ አባላትም ከህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤት አባልነት እራሳቸውን በማግለል ምክር ቤቱ ሥራውን መቀጠል እንዳይችል ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

የወታደራዊው ምክር ቤትም በህገ መንግስት የማርቀቅ ሂደት የአባልነት ጉዳይ ላይ የተከሰተውን ችግር ለመቅረፍ ባደረገው ጥረት ከምክር ቤት አባልነት እራሳቸውን ያገለሉ አካላት ወደ ምክር ቤቱ እንዲመለሱና በምላሹም ፓርላማውም ሆነ የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ ከሃይማኖት አገዛዝ ተፅዕኖ ነፃ /non-theocratic/ መሆኑን ማረጋገጫ እንዲሰጡ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ በመጨረሻ የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ የአባላት ምርጫ ወታደራዊ ምክር ቤት ቀደም ሲል ያወጣውን ህገ መንግስት የማርቀቅ ደንብ /constitutional declaration/ የሚፃረር መሆኑን በመግለፅ የግብፅ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በምክር ቤቱ ላይ ሙሉ በሙሉ እገዳ ጥሎበታል፡፡

ይህንኑ እገዳ ተከትሎም አዲስና የሁሉንም ወገን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤት ለማቋቋም በሚቻልበት ሁኔታ ዙሪያ ሰፊ የሆነ የምክክር

ሥራ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን እ.ኤ.አ ሚያዚያ 28 ቀን 2012 አዲስ የምክር ቤት ማቋቋሚያ  መመሪያ ይፋ ተደርጓል፡፡

አዲሱ መመሪያ የምክር ቤቱን አባላት የሚመርጥበት አሰራር ቀድሞ ከነበረው አሠራር የተለየ መሆኑንና በቀደመው ህግ ከፓርላማ ውጪ የሚመረጡ አባላት በፓርላማው የሚመረጡበት አካሄድ ተቀይሮ አባላቱ በራሳቸው በተቋማቱ መመረጥ እንደሚገባቸው ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የፓርላማ አባላት ይወክሉናል ብለው የሚያምኑባቸውን 37 ተወካዮች እንዲመርጡ፣ ከእምነት ተቋማት መሀከል የግብፅ ዋነኛ የእስልምና ተቋም (Al-Azhar) አራት ተወካዮችን፣ የCoptic፣ የካቶሊክና የAnglican ዐብያተ ክርስቲያናት በጋራ ስድስት ተወካዮችን እንዲመርጡ ይፋ የተደረገው መመሪያ ደንግጓል፡፡

አስር ያህል የምክር ቤቱ አባላት በህግና በህገ መንግስት ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች መሆን እንዳለባቸው የሚጠቁመው መመሪያው እያንዳንዱ የህግ ተርጓሚ አካል አንድ አንድ ተወካይ እንዲመርጥ ወስኗል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ገበሬዎችና ሠራተኞች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካዮች እንዲኖራቸው የተወሰነ ሲሆን ተማሪዎች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ታዋቂ ግለሰቦች በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲወከሉ መመሪያው ያዛል፡፡

በዚሁ መሠረት ቀደም ሲል ሲያወዛግብ ከቆየው የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን የአባልነት ድርሻ በተለየ ሁኔታ በአዲሱ መመሪያ 63 ያህል የምክር ቤቱ መቀመጫዎች ከፓርላማው ውጪ ለሆኑ አካላት የተሰጡ ሲሆን በምክር ቤቱ የሚታቀፉ ተቋማት የሚወክሏቸውን አካላት ለመምረጥም ሆነ ምክር ቤቱ በመጨረሻ የሚያረቀው ህገ መንግስት በጋራ መግባባት /consensus/ ውሳኔ ማግኘት እንደሚኖርባቸው መመሪያው ያዛል፡፡

በሚረቀቀው ህገ መንግስት አንቀጾች ላይ የሚደረጉ ውሳኔዎች የጋራ መግባባት ላይ የማይደረስባቸው ከሆነም በሁለት ሶስተኛ ድምጽ እንዲያልፉ እንደሚደረግ ይኸው

የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረም ከምክር ቤት አባላቱ የ57 ያህሉን ድጋፍ ማግኘት በቂ እንደሚሆን መመሪያው ያስቀምጣል፡፡

መመሪያው በመጨረሻም የህገ መንግስት አርቃቂ ምክር ቤቱ አዲሱን የሀገሪቱን ህገ መንግስት የማርቀቁን ተግባር የግብፅ ሁለተኛ ዙር ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ይካሄድበታል ተብሎ ከተያዘው እ.ኤ.አ ከሰኔ 16-17 ቀን 2012 በፊት ማጠናቀቅ እንደሚኖርበት ቀነ ገደብ አስቀምጧል፡፡

ይሁን እንጂ የፕሬዚዳንታዊው ምርጫ የሚካሄድበት ቀን ከመቃረቡና ምክር ቤቱ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት መዋቀር ካለመቻሉ የተነሳ ይህ ውሳኔ ተግባራዊ የመሆኑ ጉዳይ በብዙዎች ዘንድ ጥርጣሬን ያስከተለና ለብዙ መላምቶች በር የከፈተ ጉዳይ መሆኑን ዘገባዎች ያመለክታሉ፡፡

## የግብፅ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ

እ.ኤ.አ ግንቦት 23 እና 24 ቀን 2012 በግብፅ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቀው የመጀመሪያው ዙር እንዲሁም እ.ኤ.አ ሰኔ 16 እና 17 ቀን 2012 የሚደረገው ሁለተኛው ዙር የፕሬዚዳንት ምርጫ የብዙዎችን ትኩረት የሳበ ጉዳይ ሆኗል፡፡ የግብፅ የፕሬዚዳንት ምርጫ ቀደም ሲል ከታሰበው በተለየ ሁኔታ በውጥረት የተሞላና በየዕለቱ በሚፈጠሩና ምናልባትም የሀገሪቱን የፖለቲካ አለመረጋጋት ወደባሰ ቀውስ በሚከቱ ሁነቶች እየታጀበ መምጣቱ ይስተዋላል፡፡

በግብፅ የፕሬዚዳንትነት ዕጩ ማሳወቂያ የጊዜ ገደብ ሃያ ሶስት ያህል ተወዳዳሪዎች እራሳቸውን በዕጩነት አቅርበው የነበረ ቢሆንም የግብፅ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት /Egypt's administrative court/ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 18 ቀን 2012 ባስተላለፈው ብይን አስር ያህል ዕጩዎች በውድድሩ እንዳይሳተፉ ወስኗል፡፡

የግብፅ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይህንን ብይን ከመስጠቱ አስቀድሞ የFreedom and Justice Party የወታደራዊው ምክር ቤት ፕሬዚዳንታዊ ዕጩ ለማቅረብ እያሴረ ነው ሲል የሰጠው መግለጫ ከወታደራዊው ምክር ቤት ጋር ከፍተኛ እሰጥ አገባ ውስጥ

ከቶት የነበረ መሆኑ ይታወሳል። ወታደራዊው ምክር ቤት በበኩሉ ለዚሁ የFreedom and Justice Party መግለጫ በሰጠው ምላሽ ምክር ቤቱ ለማንም ያልወገነ መሆኑን በመጥቀስ ካለፉት ስህተቶች መማር ጠቃሚ ይሆናል ሲል አስጠንቅቋል።

ይህ የወታደራዊ ምክር ቤት ማስጠንቀቂያ እ.ኤ.አ በ1954 በግብፅ በMuslim Brotherhood ላይ የተወሰደውን እርምጃ የሚያጣቅስና ወታደራዊው ምክር ቤት ስልጣኑን በኃይል ለማረጋገጥ ያለውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ተችተውታል።

የFreedom and Justice Partyም ከዚሁ ፍራቻ በመነጨ በሚመስል መልኩ ቀደም ሲል በፕሬዚዳንትነት ምርጫ ውድድር ውስጥ ላለመሳተፍ የገባውን ቃል በማጠፍ የራሱን ዕጩዎች አቅርቧል።

በሌላ ሁኔታ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ሙባረክ የደህንነት ኃላፊ የነበሩት Omar Suleiman ወደ ፕሬዚዳንትነት ውድድሩ ብቅ ማለታቸው የወታደራዊው ምክር ቤት ስልጣኑን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አይደለም የሚሉ ወገኖችን ጥርጣሬ ከፍ አድርጎት ቆይቷል።

ይሁን እንጂ የግብፅ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ ሚያዚያ 18 ቀን 2012 ባስተላለፈው ብይን የFreedom and Justice Party የመጀመሪያ ዕጩ ሆነው የቀረቡትን Khairat el-shater በቀድሞው አገዛዝ ጊዜ የእስር ሪከርድ የነበራቸው መሆኑን በመጥቀስ ከውድድር አግዷቸዋል።

በተመሳሳይም የቀድሞው ፕሬዚዳንት ሙባረክ የደህንነት ኃላፊ የነበሩት Omar Suleiman ማሰባሰብ ይገባቸው የነበረውን ፊርማ አሟልተው ማቅረብ ባለመቻላቸው እንዲሁም የAl-Nour ፓርቲ ዕጩ የነበሩት Hazem Salah Abu Ismail ወላጅ እናታቸው የአሜሪካ ዜግነት እንደነበራቸው ተጠቅሶ ከውድድር ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከእነዚህ ሶስት ዋና ዋና ተቀናቃኞች ባሻገር ሰባት ያህል ዕጩዎች ከተወዳዳሪነት እንዲሰረዙ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት አስራ ሶስት ተወዳዳሪዎች እ.ኤ.አ

ግንቦት 23 እና 24 ለሚደረገው የፕሬዚዳንትነት ምርጫ ዘመቻቸውን ጀምረዋል፡፡ ከእነዚህ መሀከል በፕሬዚዳንት ሙባረክ የመጨረሻ የሥልጣን ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉት Ahmed Shafiq በምርጫ ኮሚሽኑ ተጥሎባቸው የነበረው እገዳ ተነስቶ እንዲወዳደሩ ፍቃድ በማግኘታቸው የፕሬዚዳንትነት ውድድሩ የተለየ ትኩረት እንዲያገኝ አድርገውታል፡፡

የFreedom and Justice Party በወታደራዊው ምክር ቤት ላይ ያለው ጥርጣሬ እጅግ ሥር የሰደደ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ እንዲሁም ፓርቲው ባልተጠበቀ ሁኔታ ያገኛቸውን ፖለቲካዊ ዕድሎች የበለጠ ለማጠናከር ካደረበት ፅኑ ፍላጎት በመነጨ ቀደም ሲል የገባውን ቃል በማጠፍ በፕሬዚዳንትነት ምርጫው ዕጩ ማቅረቡ ፓርቲው የስልጣን መንበሩን የበለጠ ለመቆናጠጥና በግብፅ የፖለቲካ መድረክ ዋና ተዋናይ ለመሆን ያለውን ስትራቴጂ ያመለክታል የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች ብዙ ናቸው፡፡

የፖለቲካ ተንታኞቹ ሀሳባቸውን ሲያጠናክሩም፤ ፓርቲው በመጀመሪያ ያቀረባቸው ዕጩ በፍርድ ቤት እገዳ ሊጣልባቸው እንደሚችል አስቀድሞ በመተንበይና ዝግጅት በማድረግ ተለዋጭ እጩ ያስመዘገበ መሆኑን፤ በመጨረሻም የel-shater ዕገዳ ይፋ ሲሆን የፓርቲው ሊቀመንበር የሆኑትን Mohamed Morsiን በዕጩነት እንዲወዳደሩ ማድረጉን ይጠቅሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ Mohamed Morsi በብዙዎች ዘንድ ከel-shater ያነሰ የፖለቲካ ጥንካሬ ያላቸው እንደሆኑ እየተነገረ ይገኛል፡፡

የግብፅ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ የፕሬዚዳንትነት ውድድሩን አጠቃላይ አቅጣጫ የለወጠው መሆኑን የሚናገሩት የፖለቲካ ተንታኞች ከዚህ የፖለቲካ ውጣ ውረድ በዋናነት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ሌሎች ዕጩዎች፤ የቀድሞው የአረብ ሊግ ሊቀመንበር Amr Moussa እና የለዘብተኛ አስተሳሰብ አራማጅ የሆኑት የቀድሞው የMuslim Brotherhood አባልና እራሳቸውን ፕሬዚዳታዊ ዕጩ አድርገው በማቅረባቸው ሳቢያ ከፓርቲው የተባረሩት Abdul Moniem Abul Fotouh እንደሚሆኑ እየተነበዩ ይገኛሉ፡፡

የFreedom and Justice Party ቀድሞ የገባውን ቃል ማጠፉና በፕሬዚዳንት ምርጫው ለመሳተፍ መወሰኑ ያላስደሰታቸው የፓርቲው አባላት ለቀድሞ አባላቸው Abul Fotouh ድጋፋቸውን ይሰጣሉ የሚል ግምት ያለ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር Abul Fotouh የሳላፊ እስልምና ፍልስፍና አራማጅ የሆኑና በፓርላማው ውስጥ ከFreedom and Justice Party ቀጥሎ ከፍተኛ ድምፅ ያገኙትን Al-Nour Party, Asala እና Building and Development ፓርቲዎችን እንዲሁም በፕሬዚዳንት ሳዳት ላይ የግድያ ሙከራ ማድረጉ የሚጠቀስለትና በአሁኑ ወቅት ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ መድረኩ የተቀላቀለውን Gamaat Islamiya ፓርቲን ይሁንታ ማግኘታቸው በፕሬዚዳንትነት ውድድሩ ከፍተኛ ግምት እንዲሰጣቸው ማድረጉ ይጠቀሳል፡፡ በቅርቡ ይፋ በተደረጉ የህዝብ አስተያየት መለኪያዎችም Abul Fotouh ከዚህ ቀደም Amr Mossa የነበራቸውን የድምፅ ብልጫ በማጥበብ ወደ ተቀናቃኝነት ደረጃ መሸጋገራቸው ይህንኑ የሚያሳይ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ እ.ኤ.አ በመጪው ግንቦት 23 እና 24 ቀን 2012 በግብፅ በሚካሄደው የፕሬዚዳንት ምርጫ ላይ በዋና ተቀናቃኝነት የተፈረጁት አራት ዕጩዎች መሆናቸውን በተደጋጋሚ ከሚወጡ ዘገባዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን እነዚህም፤ በቀድሞው ፕሬዚዳንት ሙባረክ ዘመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኋላም የአረብ ሊግ ሊቀመንበር የነበሩት Amr Moussa፣ የMuslim Brotherhood ተወካይ Mohamed Morsi እንዲሁም በግል ለመወዳደር የቀረቡትና በኋላም የሳላፊስት እስልምና አራማጅ የሆኑትን ጨምሮ የሌሎች ፓርቲዎችን ድጋፍና ይሁንታ ያገኙት Abdul Moniem Abul Fotouh ናቸው፡፡

በፕሬዚዳንት ሙባረክ የመጨረሻ የሥልጣን ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩትና የግብጽ አየር ኃይል ኮማንደር የነበሩት Ahmed Shafiq ወደ ውድድሩ መቀላቀላቸውን ተከትሎም በበዙዎች ዘንድ የወታደራዊው ምክር ቤት ድጋፍ

አላቸው የሚል ጥርጣሬ ማሳደሩንና ይኸውም ምርጫውን የበለጠ ተጠባቂ ሊያደርገው እንደሚችል እየተገለጸ ይገኛል፡፡

## የፕሬዚዳንታዊ ፓርቲዎችና ዕጩዎች አቋምና አጠቃላይ የምርጫ እንቅስቃሴ ዳሰሳ

በግብፅ የፕሬዚዳንትነት ምርጫ ዕጩ ሆነው የቀረቡና ከፍተኛ ግምት የተሠጣቸው ተወዳዳሪዎች ከሚያራምዷቸው የውጪ ፖሊሲዎች መሀከል በሁሉም ዘንድ እየተጠቀሰ የሚገኘው የጋራ ጉዳይ ግብፅ በአካባቢያዊም ሆነ በዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያላት ተሠሚነት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን፤ ሀገሪቱም በእነዚህ መድረኮች የሚገባትን ቦታ ማግኘት አለመቻሏን የሚመለከተው ዋናው ጉዳይ ነው፡፡

ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ መነሻ በማድረግ የFreedom and Justice Party ያወጣውን የእ.ኤ.አ. የ2011 የምርጫ ፕሮግራም ስንቃኝ በዋናነት በቀድሞው ፕሬዚዳንት ሙባረክ ዘመን ግብፅ በአካባቢያዊም ሆነ በዓለም አቀፋዊ መድረኮች የነበራት ተሠሚነት በአሳፋሪ ሁኔታ መቀነሱን፤ የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ስምምነትንም በሚገባ መቆጣጠር እንደተሳናት ያስቀምጣል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ፓርቲው ትኩረት ሠጥቶ ከሚንቀሳቀስባቸው ጉዳዮች መሀከል በብሔራዊ የፀጥታና ለሀገሪቱ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሥራት እንደሚገኝበት በመጥቀስ ከነዚህ መሀከል የዓባይ ውኃ አጠቃቀም እንዲሁም የሶማሊያ፣ የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ጉዳዮች እንደሚገኙበት በግልፅ አስቀምጧል፡፡

የቀድሞው የዓረብ ሊግ ሊቀመንበርና በውድድሩ ከፍተኛ ግምት እየተሰጣቸው የሚገኙት Amr Moussa በበኩላቸው የግብፅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላለፉት አያሌ ዓመታት ውድቀት አጋጥሞት የነበረ መሆኑንና ሀገሪቱን ወደሚገባት መድረክ ለመመለስ ፖሊሲው ዳግሞ ሊቀረፅ እንደሚገባው በምርጫ ዘመቻቸው ደጋግመው ሲጠቀሱ ተሰምቷል፡፡

Amr. Mossa በምርጫ እንቅስቃሴያቸው በተደጋጋሚ የሚታወቁበት ሌላው ጉዳይ ኢ.ኤ.አ በ1979 በሀገራቸውና በእስራኤል መሀከል በተፈረመው የCamp David ስምምነት ላይ በሚሰነዝሩት ነቀፌታ ሲሆን በእስካሁኑ ሂደት ይህ አቋማቸው ሰፊ ድጋፍ እያስገኘላቸው እንደሆነ ለመረዳት ይችላል፡፡

የሳላፊ እምነት አራማጅ ፓርቲዎች በተመሳሳይ በግብፅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ሀገሪቱ በአካባቢያዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ መድረኮች የነበራትን ቦታ በሚመለከት ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር የሚመሳሰል አቋም እያራመዱ እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

## የፕሬዚዳንታዊ ዕጩዎች የድጋፍ ሁኔታ

በግብፅ የፓርላማ ምርጫዎች ከፍተኛ መቀመጫ በማግኘትና በፖለቲካው መድረክ ዋነኛ ተፎካካሪ ሆኖ የቀረበው የMuslim Brotherhood የፖለቲካ ክንፍ የሆነው የFreedom and Justice Party ተወካይ Mohammed Mursi ፓርቲያቸው ካለው ከፍተኛ ድጋፍና የረጅም ጊዜ የማኅበራዊ አገልግሎት ልምድ የተነሳ አሸናፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት ተሰጥቷቸው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በMuslim Brotherhood የተለያዩ አካላት፣ በተለይም በወጣት የድርጅቱ አባላት ዘንድ የተነሳው ፓርቲውን በዘመናዊ አደረጃጀት የማዋቀር ጥያቄ፤ ፓርቲው ቀደም ሲል ፕሬዚዳንታዊ ዕጩ ላለማቅረብ የገባውን ቃል በማጠፉ በተፈጠረ ቅሬታ እንዲሁም ፓርቲው ለረጅም ጊዜ የሚታወቅበትን የማኅበራዊ አገልግሎት አሰጣጥና የኢኮኖሚ ድጋፍ እንቅስቃሴ ወደጎን በመተው በፖለቲካና በሥልጣን መቆናጠጥ ጉዳዮች ላይ እያተኮረ ይገኛል በሚሉ ቅሬታዎች ሳቢያ በፓርቲው መሀከል

ልዩነቶች መፈጠራቸው Mohammed Mursi ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፍ እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይገልፃሉ።

በፕሬዚዳንታዊ ውድድሩ ከፍተኛ ግምት ከተሠጣቸው ሌሎች ተወዳዳሪዎች መሀከል የMuslim Brotherhood የቀድሞ አባልና ለዘብተኛ አቋም እንደሚያራምዱ የሚነገርላቸው Abdul Moniem Abul Fotouh ዋና ተጠቃሽ ናቸው።

Abul Fotouh በፓርላማ ምክር ቤቶች ውስጥ በአስገራሚ ሁኔታ ከFreedom and Justice Party ቀጥሎ ከፍተኛ መቀመጫ ያገኘውን የሳላፊ እስልምና ዕምነት አራማጅ የሆነውን የAl-Nour ፓርቲን እንዲሁም Al-Gama’a Islamiya፣ የAl-Wasat እና Wael Ghonim ፓቲዎችን ድጋፍ ማግኘታቸው በውድድሩ ከፍተኛ ግምት እንዲሰጣቸው አድርጓል።

Abul Fotouh በተጨማሪም በMuslim Brotherhood ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባት በተለይ የድርጅቱን ወጣት አባላት ድምፅ ሊያገኙ እንደሚችሉና ይህም ምርጫውን በአሸናፊነት ለመወጣት ዕድል ሊሰጣቸው እንደሚችል እየተተነበየ ይገኛል።

በፕሬዚዳንት ሙባረክ ዘመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና በኋላም የዓረብ ሊግ ሊቀመንበር ሆነው ያገለገሉት፤ እራሳቸውንም የነፃና ብሔራዊ አስተሳሰብ /secular nationalistic/ አራማጅ አድርገው የሚያቀርቡት Amr Moussa ካላቸው ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ ልምድና በሊበራል አስተሳሰብ እንዲሁም በኮፕቲክ የክርስትና እምነት አራማጆች ተከታዮች ዘንድ ካላቸው ተቀባይነት የተነሳ ምርጫውን በአሸናፊነት ሊያጠናቅቁ የሚችሉበት ዕድል እንደሚኖር የፖለቲካ ተንታኞች ይገልፃሉ።

ይሁን እንጂ Amr Moussa በፕሬዚዳንት ሙባረክ ዘመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ማገልገላቸው፣ የግብፅ አብዮት ጅማሬ ላይ ለፕሬዚዳንት ሙባረክ አሳይተውት የነበረው ድጋፍ እንዲሁም በአብዮቱ ሂደት ዘላቂ (consistent) የሆነ አቋም

ማራመድ ሳይችሉ መቅረታቸው በአሉታዊነት እየተጠቀሰባቸው እንደሚገኝ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ዕጩው የወታደራዊ ምክር ቤቱን አገዛዝ በተመለከተ እንደ Muslim Brotherhood እና Salafist ተወካዮች ግልፅ ተቃውሞ ማሰማት አለመቻላቸው የወታደራዊው ምክር ቤት ድብቅ ድጋፍ እንዳላቸውና የቀድሞ አገዛዝ አስተሳሰብ አራማጅ ተደርገው እንዲፈረጁ አድርጓቸዋል፡፡

በፕሬዚዳነት ሙባረክ የመጨረሻ የሥልጣን ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር ሁነው ያገለገሉትና የፕሬዚዳነታዊ ምርጫ ውድድሩን እንዲቀላቀሉ የተፈቀደላቸው Ahmed Shafiqም የወታደራዊውን ምክር ቤት ድጋፍ ሊያገኙ እንደሚችሉና በምርጫው ከፍተኛ ተፎካካሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ እየተነገረ ይገኛል፡፡

Ahmed Shafiq የግብጽ ፓርላማ አውጥቶት እና የወታደራዊው ምክርቤት አጽድቆት በነበረው በፕሬዚዳንት ሙባረክ ዘመን በከፍተኛ የሥልጣን ደረጃ ያገለገሉ ባለሥልጣናት በፕሬዚዳንታዊ ምርጫው እንዳይሳተፉ በሚከለክለው ህግ መነሻነት ከውድድሩ ታግደው የነበረና በይግባኝ ወደ ውድድሩ መመለሳቸው እንዲሁም የግብጽ አየር ኃይል ሆነው ማገልገላቸው ከወታደራዊው ምክር ቤት ጋር ቁርኝት እንዳላቸውና እንደ Amr Moussa ሁሉ የቀድሞው አገዛዝ አስተሳሰብ አራማጅ ተደርገው እንዲፈረጁ አድርጓቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የተወዳዳሪዎች የፖሊሲ አቋምና ከበስተጀርባቸው ሊያሠልፉቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ አካላት ሲቃኙ ለዘብተኛ አቋም የሚያራምዱትና የቀድሞው የMuslim Brotherhood አባል የነበሩት Abul Fotouh እና እራሳቸውን የነጻና ብሔራዊ አስተሳሰብ አራማጅ አድርገው የሚያቀርቡት Amr Moussa በውድድሩ ጎልተው እንደሚወጡ ፥ የMuslim Brotherhood ተወካይ እና የሳላፊ ኃይሎች ተወካዮች በምርጫው ሊያገኙ የሚችሉት ድጋፍ የተከፋፈለ እንደሚሆንና በመጨረሻም Amr

Moussa እና Abul Fotouh ወደ ሁለተኛው ዙር የምርጫ ውድድር ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ የፖለቲካ ተንታኞቹ እየገለፁ ይገኛሉ።

**በግብፅ የፖለቲካ ሁኔታ ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች**

የግብፅ የፖለቲካ ሁኔታ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት በየዕለቱ የሚከሰቱ ጉዳዮች ማህበረሰቡን ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ እየከተቱት እንደሚገኙ እየተገለፀ ይገኛል።

ከእነዚህ መሀከል በህብረተሰቡ እና በፀጥታ ኃይሎች መሀከል የሚደረጉትና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደጉ የመጡት ግጭቶች፣ መንስኤዎችና ከበስተጀርባቸው ያሉ አካላት፣ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ይጠናቀቃል ተብሎ ዕቅድ ተይዞለት የነበረው ህገ መንግስት ከቶውንም አለመጀመሩ፣ ወታደራዊው አገዛዝ ከኢኮኖሚው ያለው ተጠቃሚነት ሳይነካና የስልጣን መንበሩን በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ካስረከበ በኋላ የሚኖረው ዕጣ ፈንታ ሳይስተጓጎል ስልጣን የመልቀቁ እውነታ የሚኖረው ተጨባጭነት እንዲሁም የተመራጩ ፕሬዚዳንትና የፓርላማው የሥልጣን ወሰን በግልፅ አለመቀመጥ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሂደት ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባና የወታደራዊውን ምክር ቤት ሥልጣን የማስረከብ ዝግጁነት ጥያቄ ውስጥ የከተቱ ጉዳዮች መሆናቸውን ከተለያዩ ዘገባዎች ለመረዳት ይቻላል።

**የግብፅ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤትና ከሀገራችን አኳያ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች**

በግብፅ የፕሬዚዳንትነት ምርጫ በዋና ተቀናቃኝነት የተፈረጁት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከሚያራምዱት የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዲሁም ከበስተጀርባቸው ካሰለፏቸው ኃይሎች በመነሳት በውጤቱ አሸናፊ ሆነው መውጣት ከቻሉ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከሚታዩ ክስተቶች እንዲሁም ከዓባይ ወንዝ አጠቃቀም

ጋር በተያያዘ ከሀገራችን አንፃር በግልፅ ሊያራምዷቸው የሚችሏቸው ፖሊሲዎችና አስተሳሰቦች እንደሚኖሩ እሙን ነው፡፡

የግብፅ የፖለቲካ ሁኔታ ሲዳሰስ በተለይ ከሀገራችን ጋር በቀጥታ የሚያቀራኘው ጉዳይ የዓባይ ወንዝ የውኃ አጠቃቀም እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ የሚታመን ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት ግብፃውያን የዓባይ ወንዝን በሚመለከት እ.ኤ.አ. በ1929 እና በ1959 በወቅቱ ሀገሪቱን በቅኝ ግዛትነት ታስተዳድር ከነበረችው እንግሊዝ ጋር የተፈራረሙት ውል ፀንቶ እንዲቆይ በተለያዩ መልኮች ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ እ.ኤ.አ. በ1999 በተመሠረተው የNile Basin Initiative መድረክ አማካኝነት የላይኛው እና የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ለረጅም ጊዜ ድርድር ሲያካሂዱ ቆይተው ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ እና ታንዛኒያ፣ እ.ኤ.አ. በ2010፥ በኋላም ቡሩንዲ የዓባይ ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን መፈራረማቸው ይታወሳል፡፡

ይህ ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ የዓባይ ውኃ አጠቃቀምን በሚመለከት በኢትዮጵያና ግብፅ መሀከል ይፈጠራሉ ተብለው የሚታሰቡ የግንኙነት አውታሮችን በሶስት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል በዘርፉ ጠለቅ ያለ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እየጠቀሱ የሚገኙት ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህ የግንኙነት አውታሮችም፡-

1. በውኃ አጠቃቀም ረገድ በሁለቱ ሀገራት መሀከል የሚከሰት ግጭት
2. የነጭ ዓባይ ጥምረት (White Nile Coalition) እና
3. የኢትዮ-ግብፅ ትብብር ናቸው፡፡

በውኃ አጠቃቀም ረገድ በሁለቱ ሀገራት መሀከል ሊከሰት የሚችል ግጭትን በሚመለከት፣ ይህ ሁኔታ ሊከሰትበት የሚችልበት ዕድል እጅግ የጠበበ መሆኑን የሚናገሩት ምሁራን ግጭት የሚከሰትበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን የግጭቱ ጀማሪ ግብፅ እንደምትሆን፤ በዚህም ሀገሪቱን ከፍተኛ ዋጋ /resource/ እንደሚያስወጣትና ለተጨማሪ አለመረጋጋት መንስዔ እንደሚያደርጋት፣ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ የነበራትን ድጋፍና በውኃ ሀብት ክፍፍል ተጐጂ እንደምትሆን ለረጅም ጊዜ ስታራምደው በቆየችው አቋም የገነባችውን የሞራል የበላይነት እንደሚያሳጣት እነዚሁ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል በግጭቶች ሳቢያ የሚከሰቱ አለመረጋጋቶች ብሔራዊ ስሜትን የመፍጠር ሚና ሊኖራቸውና ኅብረተሰቡን የማነሳሻ አንድ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል፣ ይህንንም አንዳንድ የግብፅ ፖለቲከኞች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ቢጠቆምም እስካሁን ድረስ በይፋ ከሚታየው እንቅስቃሴ የግብፅ ፖለቲካ ለጊዜውም ቢሆን በሀገር ውስጥ ጉዳዮችና በግብፅና እስራኤል ግንኙነት ዙሪያ የሚሽከረከር መሆኑን ማስተዋል ተችሏል፡፡

የነጭ አባይ ተፋሰስ ጥምረትን በሚመለከት የወታደራዊው የበላይ ምክር ቤት ከፕሬዚዳንት ሙባረክ አገዛዝ የተለየ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ እያካሄደ እንደሚገኝና ይህንን መሠል እንቅስቃሴም ግብፅ በዋናው የናይል ተፋሰስ ሀገራት ማዕቀፍ ውስጥ የራሷን ፍላጐትና ስትራቴጂ ለማራመድ ልትጠቀምበት እንደምትችል እየተጠቀሰ ይገኛል፡፡

ይህ የነጭ ዓባይ ተፋሰስ ጥምረት ግብፅ በዩጋንዳ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና በተለያዩ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ዘርፎች የጀመረቻቸውን እንቅስቃሴዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚደረግ ትንበያ ሲሆን ይህ ጥምረት ይፋዊም ሆነ ይፋዊ ባልሆነ መንገድ ሊደረግ እንደሚችል

ተጠቁሟል፡፡ ይህ ጥምረት እውን ከሆነም የዓባይ ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ተግባራዊ እንዳይደረግ የበኩሉን ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ረገድ የኮንጎ ሪፐብሊክ የዐባይ ስምምነትን አለመፈረም፣ እንዲሁም ደቡብ ሱዳን በስምምነቱ ላይ ያላት አቋም ይፋ አለመሆን ለጥርጣሬው መነልበት አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን መረጃዎቹ ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የዐባይ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ፈራሚ ከሆኑ ሀገራት መሀከል ኢትዮጵያና ዩጋንዳ በግብጽ የተረጋጋ መንግስት እስኪመሰረት ድረስ ስምምነቱን በየሀገሮቻቸው ፓርላማዎች ላለማጸደቅ የገቧቸውን ቃሎች ግብጽ በተለየ ትርጋሜ በመጠቀም የሀገራቱን ህብረት ለመከፋፈል እየተንቀሳቀሰችባቸው መሆኑን እኒሁ መረጃዎች ለአብነት የሚጠቀሱት ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በመጪዎቹ ዓመታት በግብፅ የሚኖረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ በፕሬዚዳንት ሙባረክ አገዛዝ ወቅት ለረጅም ጊዜ ሰፍኖ ከነበረው ፖለቲካዊ መረጋጋት የተለየ መልክ እንደሚኖረው የሚናገሩት የፖለቲካ ተንታኞች ለዚህ ማስረጃም ሀገሪቱ ከእስራኤልና ሳዑዲ ዓረቢያ ጋር የጀመረችውን እስጥ አገባ እንዲሁም ከኢራን ጋር በመካከለኛ ደረጃ የጀመረቻቸውን ግንኙነቶች ከምዕራቡ ዓለም ጋር በሚኖራት ግንኙነት ላይ የሚያሳርፈውን ጫና በምሳሌነት ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህ እሰጥ አገባዎችና ግንኙነቶች በወደፊቱ የሀገሪቱና የመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የፖለቲካ መረጋጋት ላይ የበኩላቸውን ተፅዕኖ ሊያሳድሩና የግብፅን ትኩረትና ሀብት ሙሉ በሙሉ ሊስቡ እንደሚችሉም እየተገመተ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት የበለጠ ተግባራዊነቱ እየታየ የመጣው ሶስተኛው የግንኙነት አውታር፤ የኢትዮ-ግብፅ ትብብር መሆኑን የሚናገሩት በዘርፉ የተሠማሩት ምሁራን በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ የመጣውን የግብፅ ኢንቨስትመንት፣ ሀገራቱ በንግድ፣ ኢንቨስትመንትና በቴክኒክ ትብብር ረገድ እያደረጓቸው ያሉ ግንኙነቶችን እንዲሁም የግብፅ መንግሥት በዓባይ ወንዝ ግንባታ

ረገድ በኢትዮጵያ በኩል የቀረበውን ፕሮፖዛል በመቀበል በኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን የሶስትዮሽ የቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ መሳተፍ መጀመሩን እንደአብነት ይጠቅሳሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር ግብፅ ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገው የሁለትዮሽ ትብብር ከዓባይ ተፋሰስ ማዕቀፍ ይልቅ የበለጠ ጥቅም እንደሚያስገኝላት በማሰብ ከኢትዮጵያ ጋር በተሻለ መስራቱን እንደ አማራጭ መውሰዷ አይቀሬ ይሆናል ሲሉ እኒሁ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

## ግብፅ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖራት ተሳትፎና ከሀገራችን አኳያ የሚኖረው እንደምታ

በዓባይ ወንዝ አጠቃቀም ረገድ የግብፅ መንግሥት ከሀገራችን ጋር ሊከተል የሚችለው የግንኙነት አውታር እንደተጠበቀ ሆኖ የሶማሊያ ሁኔታ እንዲሁም የሱዳንና የደቡብ ሱዳን ግንኙነት ከሀገራችን አኳያ ተጨማሪ የግንኙነት አውታር ሊፈጠርባቸው የሚችሉ መስኮች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡

የግብፅ ዋና ዋና ፓርቲዎችና ዕጩዎች በውጭ ጉዳይ ስትራቴጂዎቻቸው ላይ ግብፅ በአካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ የነበራት ተደማጭነት መቀነሱንና ይህንንም ማጠናከር ዋነኛ ትኩረታቸው እንደሚሆን በግልፅ አመላክተዋል፡፡ ከእነዚህ የትኩረት ጉዳዮች መሀከልም የሶማሊያ አለመረጋጋት እንዲሁም የሱዳንና ደቡብ ሱዳን ግንኙነት ጐልተው የወጡ ጉዳዮች እንደሆኑ ይስተዋላል፡፡

እነዚህ አካባቢያዊ ጉዳዮች ሀገራችንን በቀጥታ የሚመለከቱ እንደመሆናቸው የግብፅ መንግሥት በእነዚህ አካባቢዎች የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሀገራችን የትኩረት አቅጣጫ መሆን እንደሚገባቸው ግልፅ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በግብፅ ፓርላማ አብላጫ ድምፅ በማግኘት ያሸነፈው የMuslim Brotherhood እንዲሁም የሳላፊስት እስልምና ዕምነት አራማጆችንና የሌሎች እስላማዊ መሠረት ያላቸው ፓርቲዎችን ድጋፍ ያገኙ ዕጩዎች ፕሬዚዳንታዊ መንበሩን የመቆጣጠር ዕድል የሚያገኙ ከሆነ ከፓርቲዎቹ መሠረታዊ ባህሪ በመነጨ መልኩ ከሀገራችን አኳያ የፅንፈኝነት አቋም ሊያራምዱ ከሚችሉ ኃይሎች ጋር መቀራረብ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ መገመት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም በሶማሊያ አለመረጋጋት የበኩላቸውን ሚና እየተጫወቱ የሚገኙ አካላትን በመደገፍ፣ በሱዳንና ደቡብ ሱዳን ግጭት ወገንተኝነትን በማንፀባረቅና ድጋፍ በመስጠት፣ ከኤርትራ መንግስት ጋር በመቀራረብና የሀገራችንን ሰላምና መረጋጋት ለማደፍረስ የሚያደርጋውን ሙከራ በማገዝ እንዲሁም የፅንፈኝነት ርዕዮትን ወደ ሀገራችን በማስገባት /Exporting extremist ideology/ እና በሀገራችን የኃይማኖት አክራሪነት እንዲስፋፋና ለረጅም ዘመናት የቆየውን ተቻችሎ የመኖር ባህል በማወክ ጸረ-ሰላም እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ይህንን መነሻ መሠረት በማድረግ በሶማሊያ ጠንካራና የተረጋጋ መንግሥት ለመፍጠር የተጀመረው ጥረት ፍሬያማ እንዲሆን ሀገራችን ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጋር ጠንካራ ሥራ መስራት እንደሚኖርባት ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት በሚገነባበትና አክራሪ ኃይሎች ዳግም ማንሰራራት እንዳይችሉ በማድረግ ረገድ ከምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት ሀገራት ጋር የተጀመረውን ሥራ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

በተመሳሳይ በሱዳንና ደቡብ ሱዳን መሀከል በአዲስ መልክ የተቀሰቀሰው ግጭትና ውጤት በየሀገራቱ የሚያስከትሏቸው ለውጦች ከሀገራችን አኳያ በጥልቀት ሊገመገሙና ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህም በሱዳን መንግስት ላይ እየደረሰ የሚገኘው ዓለም አቀፋዊ ጫና፣ ከደቡብ ሱዳን ጋር የተቀሰቀሰው ግጭት የሚያስከትለው ውጤት

እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ እያደገ የመጣው ማኀበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለአክራሪ ፅንፈኛ ፓርቲዎች ወደ ሥልጣን መምጣት ምቹ ሁኔታን ሊፈጥርና በግብፅ ከሚገኙ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ከሚያራምዱ ኃይሎች ጋር በሚመሰረት ጥምረት በሀገራችን ላይ ሊደርስ የሚችል አሉታዊ ተፅዕኖ ሊከሰት እንደሚችል መገመት ተገቢ ይሆናል፡፡

በሌላ መልኩ በደቡብ ሱዳን እየታየ ያለው የኢኮኖሚ መሽመድመድ፣ የጐሣዎች ግጭትና የማዕከላዊ መንግሥቱ ጠንካራ አስተዳደር መመስረት አለመቻል በአካባቢው አለመረጋጋት ሊፈጥር እንደሚችል፤ አክራሪ አቋም ሊያራምዱ የሚችሉ የግብፅ ኃይሎችም ይህንን ሁኔታ እንደ ወርቃማ ዕድል የሚቆጥሩበት ሁኔታ ሊፈጠርና ይህም በሀገራችን ላይ የበኩሉን ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ገምቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አዲሲቷ ደቡብ ሱዳን በNile Basin Initiative ውስጥ የሚኖራት ሚና እና በዚህም የዓባይ ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን በመፈረም ለፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ተጨማሪ ኃይል መሆን በምትችልበት ሁኔታ ላይ ጠንክሮ መስራት የግብፅ መንግስት የዐባይ ወንዝ የትብብር ማዕቀፍን ጥንካሬ ለመፈታተን ሊከተለው የሚችለውን የነጭ ዐባይ ጥምረት እንቅስቃሴን ለመመከት የሚያስችል እንደመሆኑ ለዚህ ሥራ ትኩረት መስጠቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በመጨረሻም ወታደራዊው አገዛዝ በይፋም ሆነ ይፋዊ ባልሆነ ሁኔታ የስልጣን መንበሩን ተቆናጦ የሚቀጥል ከሆነ በሽግግሩ ወቅት የተጀመሩ የሁለትዮሽ ግንኙነቶችን ለማስቀጠልና እንዲዳብሩ ለማድረግ ከፍተኛ አጋጣሚ ይፈጥራል የሚል ግምት አለ፡፡

ከዚህ አኳያም በቅርቡ በህዝብ ለህዝብ ረገድ ጠንካራ ግንኙት ለመመስረት በግብጽ በኩል ተጀምሮ ለነበረውና ወደሀገራችንም የፐብሊክ ዲፐሎማሲ ቡድን እስከመላክ የደረሰውን እንቅስቃሴ የማጠናከር ፣ ከሀገራችንም ተመሳሳይ ቡድን ወደግብጽ የሚጓዝበትና ከተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግስት አካላት እንዲሁም የህብረተሰብ

ተወካዮች ጋር ውይይት በማድረግ ከአሁኑ ጠንካራ የመረጃ መለዋወጫ ስርዓት የሚዘረጋበትን መሰረት መጣል ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በማንኛውም መልኩ የግብፅን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ወደ ተረጋጋ ደረጃ ለመመለስ ጊዜ የሚፈልግ መሆኑና የሚመሠረተው መንግሥት የቅድሚያ ትኩረት የሀገር ውስጥ ችግሮችን በመፍታት ላይ ያተኮረ ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም ከዚህ በላይ በተጠቆመው መሠረት የግብፅ መንግስት ከሚታሰበው ውጪ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሊያደርግ እንደሚችል በመገመት ሀገራችን ከግብፅ ጋር ባላት ግንኙነት አካባቢያዊ ፖለቲካን ከግምት ውስጥ ባስገባና የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን መስራት ይጠበቅባታል፡፡